# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ሚያዚያ 25 ቀን 2003 ዓ.ም.

### የዴሞክራሲ ዋስትና ለሆነው
### ነፃ ፕሬስ መታገል ሀገራዊ ግዳጅ ነው!!

ሜይ 3 የፕሬስ ነፃነት ቀን ተብሎ በአለም አቀፍ ደረጃ በየአመቱ እንዲከበር የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በወሰነው መሰረት „የ21ኛው ምዕት አመት ሚዲያ፡ አዲስ ወሰንና አዲስ ገደብ“ የተሰኘውን የዚህን አመት መርሃ ግብር በማንገብ በደመቀ ሁኔታ ከመቶ በላይ በሆኑ ሀገሮች ውስጥ በፕሬስ ተቋማት፣ በመንግሥት፣ ለሰብአዊና ለዴሞክራሲ መብቶች መከበር በሚንቀሳቀሱ በርካታ መንግሥታዊ ባልሆኑ ሕዝባዊ ድርጅቶች መግለጫዎችን በማውጣት፤ የተለያዩ ህዝባዊ ስብሰባዎችና ጥናታዊ ውይይቶችንና ሰሚናሮችን በማዘጋጀት ተከብሮ ውሏል። ይህ ቀን ከ1993 ዓ.ም. ጀምሮ የሚከበር ነው። ነፃና መድበላዊ ጠባይ ያለው ነፃ ፕሬስን መገንባትና መንከባከብ ለሲቪል ማህበረሰቡና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሀገርም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ አስፈላጊና መሠረታዊ ነው። ነፃ ፕሬስ - ሃሳብን በሆነው ዓይነት የፕሬስ መልክ በነፃ የመግለጽ መብት - በአንድ አካባቢ አደጋ ላይ ከወደቀ ሌሎች መብቶች በሙሉ ዋስትና የሌላቸው እንደሚሆኑ በርካታ ታሪካዊ ተመክሮዎች የሚገልጹትና የሚያረጋግጡት ነው። ከዚህ ግንዛቤ በመነሳት ነፃ ፕሬስ በየትም ቦታ ነጻነቱን የማጣት አደጋ እንዳያጋጥመው ነቅቶ መጠበቅና መከላከል ከማንም ሀገር ወዳድና ለህዝብ ቅን አሳቢ ከሆኑት ሁሉ የሚጠበቅ ነው። በሌለበት አካባቢ ደግሞ እንዲገነባ ቆርጦ መታገል የግዴታ ነው - ለማህበራዊ፣ለሶሻልና ለፖለቲካው ያለው አስጠዋጽኦ እጅግ ከፍ ያለና መሠረታዊም ነውና።

የዚህ ቀን ታሰቦ መዋል ዋና አላማው „ነፃ ፕሬስን አስመልክቶ“ በአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነድ በአንቀጽ 19 እንደተቀመጠው መሠረታዊ የሆኑትን የፕሬስ ነፃነት መርሆዎችን በማክበርና ከጥቃትም በመከላከል፤ የት ነበርን? የት ደርሰናል? ምንስ ይቀረናል? የተሰኙ መሠረታዊ ጥያቀዎችን በመመርመር ለተሰሩ ስህተቶች እርምት እንዲደረግ፤ በዕቅድ ተይዘው ተግባራዊ ያልሆኑ እንቅፋቶችን መርምሮ ለማስወገድ መፍትሄ እንዲፈለግ፤ ከጊዜው ጋር መሄድ የሚገባቸውን አስመልክቶ ደግሞ ለተግባራዊነታቸው ካለፈው በበለጠ ተግቶ ለመሥራት ቃል የሚገባበት ብቻ ሳይሆን ለፕሬስ ነፃነት መኖርና መከበር ሲሉ መስዋዕት የከፈሉትን የነፃ ፕሬስ አባሎችንም ለመዘከር ጭምር ነው።

እንደ ኢትዮጵያ በመሰሉ በአምባገነን ሥርዓት በወደቁ ሀገሮች የፕሬስ ነፃነት የሚከበሩ ባለመሆናቸው አንድ ዜጋ እንደ ግለሰብ የራሱን እንደ ሕዝብ ደግሞ የሀገሩን የወደፊት እጣና ዕድል ለመወሰን፡ ጥቅሜንና ፍላጎቴን ያስከብርልኛል የሚላቸውን የፖለቲካና የኤኮኖሚ ሥርዓትን ለመገንባት የሚቻል እንዳልሆነ ያለፉት 19 አመታት በወያኔ አገዛዝ ከበቂም በበቂ ግልፅ የተደረገ ነው። ማስረጃ አምጡ ብሎ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚሟገትም ከቶ ሊኖር አይችልም። የመለስ አገዛዝ ሀሳብን በነፃ ለማንሸራሸር የማይቻልበት የፖለቲካ ምህዳር በሀገራችን በማስፈኑ ሕዝባችን ለዴሞክራሲ፣ ለፍትህ፣ ለሰላምና ለልማት፣ ለመልካም አስተዳደር ግንባታ፣ ለሕግ የበላይነት መኖርና መጠበቅ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን እንዳያገኝ፣ የተደቀኑ እንቅፋቶችን እንዳያስወግድ በዋና ኃሬጣነት ተጠያቂ ነው። በመሆኑም ይህ ሁኔታ ባለበት የመለስ አገዛዝ ደጋፊዎቹ ስለ ፕሬስ ነፃነት ማውራታቸ፤ የተፃፈበትን ወረቀት ያህል እንኳ ክበደት በሌለው ሕገ-መንግሥት ተደንግጓል እያሉ ነጋ ጠባ ሕዝብን የሰለቸ ፕሮፓጋንዳ ቢያቅራሩ፤ ለሕዝባችን ለቀባሪው አረዱት ከማለት ውጭ በሌላ በምንም ሊተረጎም አይችልም። ባጭሩ ማለት የሚቻለው፤ ሁሌም እያወናበዱ መቀጠል የማይቻል መሆኑን መገንዘብ እንዳለባቸው ብቻ ነው።

ሕዝብ የማወቅና መረጃ የማግኘት መብቱ በጠመንጃ ኃይል ተዳፍኗል። ገና ከመጀመሪያውኑ በማቆጥቆጥ ላይ የነበረውን ነፃ ፕሬስ በማጥቃትና በደል በመፈፀም፤ ጋዜጠኞችን ለእስርና ግድያ ብሎም ደብዛቸው እንዲጠፉና በርካታዎችን ደግሞ እንዲሰደዱ አድርጓል። የጋዜጣና የመፅሄቶች ማተሚያ ዋጋን በመጨመር በተቻላቸው መጠን የአገዛዙን ጭካኔ ተቋቁመው ለመኖር ጥረት የሚያደርጉት ላይ የሕልውና ጥያቄ እንዲያንዣብባቸውና በግዴታ ለክስመት ዳርጓቸዋል። የራሳቸውን ነፃነት ጠብቀው በኢንተርኔት የሚወጡ ድረ-ገፆችን በማገዱም፣ በዚሁ ድርጊቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ በነፃ ፕሬስ አፋኝነት ከተመደቡት አሥር አገዛዞች ውስጥ የወያኔ አገዛዝ አንዱ ሊሆን በቅቷል። በሰሜን አፍሪካ የተቀጣጠለው የለውጥ እሳት እንዳይለበልበኝ

በሚል እንደ ፍኖተ ዴሞክራሲ ለሕዝብ የሚተላለፉ የሬዲዮ ስርጭቶችን በጠቅላላ ሀገሪቷ እንዳይሰሙ አፍኗል። ባጭሩ በኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ቀደም ሲል ጥርኝ ብርኝ ይል ከነበረበት እስከናካቴው ደብዛው የጠፋ ሁኗል።

ስለሆነም ዛሬ በአለም አቀፍ ደረጃ የፕሬስ ነፃነት ቀንን ስናከብርና መስዋዕት የከፈሉትን ጋዜጠኞችን ስንዘክር በሀገራችን ነፃ ፕሬስ እንዲኖር ገና መራር በሆነ ትግል በመለስ አገዛዝ መቃብር ላይ መመሥረት እንዳለበት ከግንዛቤ በማስገባት ነው። በተለያዩ የማጎሪያ ቤቶች ውስጥ ለእስር ተዳርገው የተለያዩ በደሎች እየተፈጸመባቸው ላሉት የነፃው ፕሬስ አባላትና የቅርብ ዘመዶቻቸው ፅናቱን እንዲሰጣቸው ብቻ ሳይሆን መብታቸውን የተገፈፉ የፖለቲካ እስረኞች ናቸውና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ እየጠየቅን ጭምርም ነው። ነፃ ፕሬስ በሌለበት፤ ሕዝብ ያለ ምንም ፍራቻ ሀሳቡን ለመግለፅ በማይችልበት፤ መልካም አስተዳደር ባልገነባበት፤ ፍላጎቱንና ጥቅሙን እንዳይገልፅ አፉ በተለጎመበት ሰላምም ሆነ ልማትና የኤኮኖሚ እድገት ሊገኝ ጨርሶ አይቻልም።

ለነፃ ፕሬስ መኖር ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በቅድሚያ ይከበሩ!!
የታሰሩ ጋዜጠኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይፈቱ!!



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France